# ቤተ ክርስቲያን በገዛ ልጆችዋ ስትፈተን!

## ቁጥር ፫

በአለፈው ቁጥር ፩ እና ፪ ላይ «የተወገዙ መምህራን ስብከት ለምን ይደመጣል» ተብሎ በተደጋጋሚ ከምእመናን ለቀረበው ጥያቄ ተገቢውን መልስ የሰጠን ይመስለናል። በዛሬው ጽሑፋችን ደግሞ «ከሀገር ባሕል መሣሪያ ውጭ በሆኑ ፤ በኦርጋን የታጀቡ መዝሙራት» ለምን በዚህ ዌብ ሳይት ላይ ይደመጣሉ ተብሎ ለተጠየቀው መልሱ እነሆ።

በመሠረቱ ይህንን ጥያቄ በቀጥታ ከመመለሳችን በፊት በቤተ ክርስቲያናችን መዝሙራትን በአማርኛ መዘመር የተጀመረው መቼ ነው? ለዚህ ጥቂት ማብራሪያ መስጠት ያስፈልጋል። ከጥንት ጀምሮ በቤተ ክርስቲያናችን ግልጋሎትና ምስጋና የሚደርሰው በግእዝ ቋንቋ ነበር። በኢትዮጵያ ወጣቶች መዝሙራትን በአማርኛ ቋንቋ እንዲዘምሩ ለመጀመሪያ ጊዜ መጽሐፍ የተዘጋጀው እ.ኢ.አ በ1940ዎቹ ላይ የመንፈሳዊ ማኅበራት (ሰንበት ት/ቤት) ገና መቋቋም እንደጀመሩ ነው (1)። በወቅቱ የነበሩት የቤተ ክርስቲያን አባቶች በሰጡት ትዕዛዝ መሠረት ወጣቱ ወደ ሌሎች ሃይማኖት እንዳይሄድ በብዛት የአማርኛ መዝሙራትን በማዘጋጀት ፤ መንፈሳዊ ማኅበራትንም በየአጥቢያው ቤተ ክርስቲያኑ እንዲቋቋሙ ከፍ ያለ ጥረት ተደርጓል። በዚያን ወቅት "እንደ ቸርነትህ"(1A) የሚለው እስከዛሬ ድረስ እጅግ ተወዳጅ የኾነው መዝሙርና ሌሎችም መዝሙሮች በአቶ ኢሳይያስ ዓለሜ የኖታ ምልክት ተደርጎላቸው ተደርሰው ፤ የቤተ ክህነቱንም ይኹኝታ አግኝተው በኦርጋን አጃቢነት መዘመር የጀመሩት ከዚያን ወቅት ማለት እ.ኢ.አ በ1946 ዓ ም ጀምሮ ነው። እነዚህም መዝሙራት ፤ ከዚያ ጊዜ አንስቶ አገበያ ላይ ውለው ማኅበራቱ ሲጠቀሙባቸው ቆይተው እስከ ዘመናችን ደርሰዋል (ለ57 ዓመታት)። በዚያን ጊዜ መዝሙራት ሲደረሱ እንዲህ እንደዛሬው ማንም ዝም ብሎ ከመሬት ተነሥቶ ዘማሪ/ዘማሪት እገሌ ብሎ በገዛ ራሱ ብቻ መዝሙር ደርሶ በካሴት ማውጣት አይችልም ነበር ፤ በቅድሚያ ለበላይ አባቶች አሳይቶና ተመርምሮ እንጂ። ለምሳሌ አቶ ኢሳይያስ ዓለሜ የመዝሙር መጽሐፋን አዘጋጅተው በኖታ ሲያቀርቡ በወቅቱ የሐረር ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስና ሌሎች ኹለት/ሦስት ሰዎችን ጨምረው አይተውና መርምረው ከፈቀዱ በኋላ ነበር የታተመው (1)። ከዚያም በኋላ የተደረሱ መዝሙራት በተመሳሳይ ሁኔታ ተመርምረው ከተፈቀዱ በኋላ ነበር በየቤተ ክርስቲያኑ የሚዘመሩት። የተደረሱትም መዝሙራት የበለጠ በሕዝብ ዘንድ እንዲታወቁና እንዲለመዱ በማሰብ ቤተ ክርስቲያናችን በ1960ዎቹ መጀመሪያ ላይ በወቅቱ ታዋቂ በነበረው አንደኛ ክፍለ ጦር በርካታ መዝሙራት በዘመናዊ መሣሪያ ታጅበው እንዲዘመሩ አድርጋ ለምዕመናን ተሰራጭተዋል (2)። እንዲሁም የሙዚቃ

ችሎታ ያላቸው ባለሙያዎች በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናቸው መዝሙራትን በዘመናዊ መሣሪያ አጅበው በመጫወት መዝሙራቱ የበለጠ ተወዳጅነትን አትርፈዋል። ይኸንንም ከፍ ያለ አስተዋፅኦ በማየት ቤተ ክርስቲያናችን ለእነዚያ የሙዚቃ መሣሪያ ተጫዋቾች የምስክር ወረቀት በመስጠት ታበረታታ ነበር (3)። ከዚህም የተነሳ አርጋኖን (ኦርጋን) በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ መገልገያ ሆኖ ቆይቷል። ከዚያ ጊዜ አንስቶም እንደ ሊቀ መዘምራን ኪነ ጥበብ እና እንደ መሪጌታ ፀሐይ ብርሃኑ ያሉት ጣእመ ዝማሬያቸው እስከ ዛሬ ድረስ ተሰምቶ የማይጠገበው ዘማርያንና ሌሎችም በአርጋኖን የታጅቡ መዝሙራትን በካሴት ስላወጡ የአማርኛ መዝሙራት ይበልጥ ታዋቂ እየሆኑ መጡ። እነዚያ በኦርጋን ታጅበው የተዘመሩ መዘሙራት ዛሬም ድረስ ምዕመናኑን ለቃለ ስብከቱ አገልግሎት ይበልጥ ለማዘጋጀት በሀገራችን በየአብያተ ክርስቲያናቱ ይዘመራሉ (4)።

ይሀ በእንዲህ እያለ ከ1980ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ በሀገር ባህል መሣሪያ እንጂ ፣ በባእድ መሣሪያ በአርጋኖን መዘመር የለበትም የሚሉ ቡድኖች ተነስተው በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ክፍፍል ስለተነሣ ፣ ይህን ችግር ለመፍታት ሲል ቅዱስ ሲኖዶስ በግንቦት ወር 1986 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መሣሪያዎች በአጃቢነት እንድንጠቀም ወስኗል፦

**ዋሽንት ፣ ከበሮ ፣ ጸናጽል ፣መሰንቆ ፣በገና ፣እምቢልታ ፣አርጋኖን/ኦርጋን** (5,6) - (ክራር ያልተፈቀደ መሣሪያ መሆኑን እዚህ ያስተውላል)። ስለ አርጋኖን ትርጓሜ በተለያዩ መዝገበ ቃላት ላይ የተገለጸውን ይመልከቱ (7)። አንዳንዶች ላለመሸነፍ ብቻ አርጋኖን ማለት አባ ጊዮርጊስ ስለ እመቤታችን ፍቅር የደረሰላት የመጽሐፉ አርጋኖን ስም ነው እንጂ መሣሪያ አይደለም ይላሉ እውነቱን ሆዳቸው እያወቀው። በመሠረቱ ሲኖዶስም መሣሪያ ባይሆን ኖሮ ከተፈቀዱ መሣሪያዎች እንደ አንዱ አድርጎ ባልቆጠረውም ነበር። ስለዚህ የእነዚህ ሰዎች ክርክር እንዲሁ የአልሸነፍም ባይነት እንጂ ፣ በቂ ማስረጃ ሊያቀርቡለት የማይችሉ በመኾናቸው ተቀባይነትም ፣ አሳማኝነትም አይኖረውም - ፈጽሞ።

## <u>ኦርጋን በቅዱስ ሲኖዶስ የተፈቀደ መሣሪያ ሆኖ ሳለ ፤ በኦርጋን መጠቀም ክልክል ነው የሚለው ሐሳብ ከየት መነጨ?</u>

የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ እንደተላለፈ ፣ በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ ሥር ነኝ የሚለው ይህ “ማኅበረ ቅዱሳን“ የውሳኔውን ትርጉም በሚፈልገው ዐይነት በማጣመም በሀገር ውስጥና በውጭና ሀገር ያሉትን ምዕምናን ለመከፋፈል ሲል በኦርጋን የሚዘምር ካለ ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባል አይደለም በማለት ትክክለኛ

ያልኾነ መመሪያ ለሰንበት ት/ቤቶች አስተላለፈ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮም በሀገር ውስጥ በሚገኙ የሰንበት ት/ቤቶች በኦርጋን መጠቀም ሲቋረጥ ፤ መስማቱ እንኳን ራሱ ፣ እንደ ኃጢአት መቈጠር ተጀመረ። በተለይ ደግሞ በኅዳር/ታኅሣሥ 1995 በሐመር መጽሔት ላይ የወጣው መርዝ የሆነ ጽሑፍ (5) ፤ ጸሐፊው ምንም ዓይነት መሠረታዊ የሆነ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ዕውቀት የሌለው ፤ ነገር ግን በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የቤተ ክርስቲያኒቱን ወይም የምእመናን አንድነት ቢቻል ለማፍረስ ባይቻል ለማናጋት ሆን ተብሎ የተጻፈ ከፋፋይ ጽሑፍ እንደነበር የወጣውን መጽሔት በመመልከት መረዳት ይቻላል። የዚህን ጽሑፍ ይዘት ከዚህ ቀጥሎ ጠቅለል ባለ መልኩ ለማሳየት እንሞክራለን፦

_*ጸሐፊው ጽሑፉን ሲጀምር መሣሪያዎቹን «ሃይማኖታዊ መሠረት ስለሌላቸው» ይልና ቀድሞ በነቢያት ቀጥሎ በሐዋርያት ከዚያም በሊቃውንት ተመስክሮላቸው እዚህ እንደደረሱ ታሪካቸውና ምስጢራቸው ያስረዳል ይላል። .....እነዚህን የዜማ መሣሪያዎች መቃወም ቀድሞ የዘመሩባቸውን ቅዱሳን ከመቃወም ተለይቶ የማይታየው ለዚህ ነው ይላል። .....በሌሎች መሣሪያዎች መዘመር ቅዱሳን አባቶችና ሊቃውንት ዜማንና የዜማ መሣሪያን በተመለከተ ካስቀመጡት የተለየ መሠረት መመሥረት ነው ይላል።*_

በብሉይ ኪዳን ሌዋውያን ካህናትም ሆኑ ሌሎች በበገና፣ በመሰንቆ፣ በእንዚራ፣ በከበሮ ወዘተ ይጫወቱ የነበረ ሲሆን እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የሙዚቃ መሣሪያዎች የተወረሱት (የተዋሱት) ከጎረቤቶቻቸው ከፋርስ፣ ከባቢሎን፣ ከአሦርና ከሚስፖታሚያ ወዘተ እንጂ የእነርሱ አይደሉም። ስለዚህ ዩባልና ልጆቹ በበገናም ሆነ በተለያዩ መሣሪያዎች ሲጫወቱ የመጀመሪያዎቹ ቢሆኑም (ዘፍ 4፥25) ለመሣሪያዎቹ ቅርጽና መልክ የሰጠው ዳዊት ነው (1010-970 B.C)። ዳዊት የኀዘንም ሆነ የደስታ መዝሙር ደራሲ በመሰንቆና በበገና ተጫዋችነቱ ይነገርለታል (አሞ 6፥5፣ 1ኛ ሳሙ 16፥16-18)። (8)

እዚህ ላይ ሊጠቀስ የሚገባው አንዳንዶች እንደሚሉት እኛ አሁን የምንጠቀምባቸው መሣሪያዎች ከኦሪቱ ጀምሮ የነበሩ ናቸው የሚሉ አልጠፉም። ነገር ግን በእኛ ዘመን ያሉ ኦሪታውያኑ አይሁዳውያን የሚጠቀሙባቸው መሣሪያዎች የእኛ ዓይነት ሳይሆኑ ቫዮሊን ፣ ኦርጋን ፤ በገና የመሳሰሉት ናቸው። ስለዚህ በኦሪት ጊዜ ይጠቀሙበት የነበረውና በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተዘረዘሩት መሣሪያዎች ማለት ዛሬ ከምንጠቀምባቸው ጋር አንድ ዓይነት ናቸው ማለት አይደለም። ነገር ግን እንደየሀገሩ ባህልና በሚያወጡት ድምፀ ቃና ስም ተጠሩ እንጂ። ለምሳሌ እኛ ከበሮ የምንለውን በእንግሊዘኛ Tambourine ወይም ደግሞ መሰንቆን Lyre ይሉታል። እንግዲህ የእነርሱ ከበሮ እንደኛ በግድ በጠፍር ካልተወጠረ የእነርሱ ትክክለኛ አይደለም ብለን መተቸት አንችልም። ለምሳሌ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ በአምስት እንጀራ 5 ሺህ ሰዎችን መገበ ስንል ምን ማለት ነው? እዚህ ላይ እንጀራ የሚለው ቃል ለእኛ ሀገር በጣም የተለመደው ስለሆነ ቃሉን ተጠቀምንበት እንጂ ፤ እሥራኤሎቹ ይመገቡት የነበረው ቂጣን የመሰለ ነገር እንጂ በትክክል እንደ እኛ አገር እንጀራ ዐይነት ነበረ ማለት አይደለም።

ብዙዎቹ መሣሪያዎች በእንግሊዘኛው ምን እንደሚባሉ ከዚህ በታች ዝርዝራቸውን ይመልከቱ ፤

1. **መለከት** Trumpet
2. **በገና** Harp (Kinnor)
3. **ከበሮ** Tambourine (Timbrel)
4. **አርጋኖን** Organ
5. **ጸናጽል** Sistrum (Cymbal)
6. **መሰንቆ** Lyres (Lyre)
7. **ጊታር** Lute
8. **ቀርነ መለከት** Shophar
9. **ነጋሪት** Castanet
10. **ዕንዚራ** Accordion
11. **ዕምቢልታ** Flute
12. **ዋሸንት** Cornet Sackbut **ናቸው።** (8)

ጽሑፉ በመቀጠልም በሐዋርያት የተመሠከረላቸው ይላል። በመሠረቱ ሐዋርያት ስለ ሙዚቃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ምንም ዓይነት የተናገሩት ነገር የለም ፣ ነገር ግን ጸሐፊው እንዲህ ዐይነት የሌለ ቃል በመደርደር ምዕመናንን ያደናግራል። እንደ ቅዱስ ያሬድ ያለው ሊቅም ቢሆን ፣ ወደ ሰማይ ተነጥቆ በተወሰደ ጊዜ «በዚያም የእንዚራን ፣ የአርጋኖን ፣ የመሰንቆን ድምጽን እንደዚሁም ሰማይና ምድርን የፈጠረ ትልቁን ንጉሥ እግዚአብሔርን ጧትና ማታ በስብሐትና በማኅሌት (በቅኔ) ጧትና በሰርክ ከፍ ባለ ዜማ ካህናተ ሰማይ መላእክት በተቀደሰ ዙፋኑ ዙሪያ ሲያመሰግኑ ሰማ.......» (9) ተብሎ ተጻፈ እንጂ በዚያ መሣሪያ የዘመረ የተወገዘ ነው አላለም። እንዲያውም ሰማይ ቤት ሰምቶ የተመሰጠበትን የአርጋኖን ድምፅ በትምህርቱ ለተማረከበት ለወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ «ሰባኬ ወንጌል ዮሐንስ ለቤተ ክርስቲያን መልካም ድምጽ የምትሰጥ በትምህርትህ የምትመስጥ የቤተ ክርስቲያን ኦርጋኖን/ኦርጋን ነህ» ብሎታል። (ዚቅ የጥር ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ እስመ ለዓለም) በተጨማሪም «የካህናቱ ምስጋና መሰንቆ አርጋኖን ሲመታ እንደሚመስጠው ድምፅ ጣፋጭ ነው» ይላል ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ። (አርያም ዘቅዱስ ያሬድ የማክሰኞ) (9)

አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫም ቢሆኑ ምስጋናቸውን በአርጋኖንና በሌሎች መሣሪያዎች መስለው እንዲህ ብለው ጽፈዋል። የእመቤታችንን ምስጋና የሆነውን መጽሐፈ አርጋኖን (10) ሲደርሱ ገና በመግቢያው ላይ «የምስጋና አርጋኖን/ኦርጋን የመዝሙር መሰንቆ እንዚራም የሚባል ይህንን መጽሐፍ እንጀምራለን ይሉና ....

የአብ ሙሽራ የሆነችውን (የድንግልን) የምስጋና መጽሐፍ መጻፍ እንድችል እርዳኝ። ለመፈጸምም እንድበቃ ሥልጣኑን ስጠኝ። ከንፈሮቼን እና አንደበቴን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በልዩ ቋንቋ ሰሚዎችን ደስ የሚያሰኝ ነገር ይናገሩ ዘንድ እንደ ኦርጋን/አርጋኖን አድርግልኝ። አንደበቴም እንደ መሰንቆ መልካም ሆኖ ይዘምር ዘንድ ምኡዝ ጣዕም ለዛ ያለው ድምጽ ይሰጥ ዘንድ ድህንፃ መንፈስ/የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንደ መሰንቆ አንደበቴን ያጫውተው (ይምታው)። ኦርጋን/አርጋኖን መሰንቆ ሰሚዎቻቸውን ደስተኛ እንደሚያደርጉ እነርሱን የሰሙ በመሣሪያዎቹ ድምጽ እንደሚመሰጡ ይህንን የእመቤታችንን ውዳሴ የሚሰሙ ኅሊናቸው ይማረክ።» (9)

አባ ጊዮርጊስ በተለያየ ስም የተጠሩት መሣሪያዎች ምን ዐይነት ድምጽ እንደሚያወጡና ምን እንደሚመስሉ «እሴብሀ ጸጋኪ» በተባለው የዘወትር የጠዋት ጸሎት ላይ እንዲህ ብለዋል። ስለ ***<u>መሰንቆ</u>*** - «ምንት ረባሑ ለመሰንቆ ለእመ አልቦ ዘይሰነቅሖ - የሚሰነቀው የሚመታው ፣የሚከረከረው ፣የሚሞዝቀው ከሌለ የመሰንቆ ጥቅሙ ምንድን ነው።» ***<u>እንዚራን</u>*** በተመለከተ ደግሞ «ወምንተ ይደምጽ ንቃወ እንዚራ ዘስቁል ለእመ ኢተነፍሀ በድግታተ ማኅሌት - (ትርጉም) የተሰቀለው እንዚራ በአንድነት ካልተነፋ የእንዚራ ድምጽ እንዴት ሊሰማ ይችላል? ብለዋል። (9) እዚህ ላይ <u>የተሰቀለው እንዚራ በአንድነት ካልተነፋ</u> የሚለው አባባል በውጭው ዓለም በትልልቅ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ፓይፐ ኦርጋን (Pipe Organ) ተብሎ የሚታወቀው ድምጹ የሚወጣው ከፍ ብሎ በሚሰቀሉት ብዙ የተለያየ የቧንቧ ቅርጽ ያላቸው በሚመስሉት ነው ፤ ታዲያ ኦርጋኑ ሲመታ በእነዚያ ቧንቧዎች ቅርጽ ባላቸው ውስጥ አየር ሲያልፍ ልዩ የሆነ ማራኪና አስገራሚ የሆነ ድምጽ ያወጣሉ።» ለዚህም ነው አባ ጊዮርጊስ አያይዘው በመቀጠል ስለ ***<u>አርጋኖን</u>*** «በነቀልቃለ ስብሐት ሑኪዮ ለአርጋኖነ ኅሊናየ ከመኢያርምም እምስብሐተ ፍቅርኪ -(ትርጉም) የፍቅርሽን ምስጋና ከማቅረብ አንደበቴ ዝም እንዳይል አርጋኖን/ኦርጋን ኅሊናዬን {ልቤን} በምስጋና ስሜት ንውጽውጽታ አንቀሳቅሺው/ አናውጪው ያሉት።» እዚህ ላይ የምንረዳው አባ ጊዮርጊስ እንዚህን መሣሪያዎችን በደንብ እንደሚያውቋቸው ነው። ኦርጋን በ14ኛው ክፍለ ዘመን በተለይ በዐፄ እስክንድር ዘመን መንግሥት ጥቅም ላይ ውሎ እንደነበር ይታወቃል። ታዲያ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የቤተ ክርስቲያናችን የዜማ መስራቾች ምስጋናቸውን በመሣሪያዎች እየመሰሉና እያደነቁ ሲደርሱ ምን ማለታቸው ነው? ለምስጋና የተሰማሙ መሆናቸውን ወይስ አሁን አንዳንዶች እንደሚሉት እንኳን ልንጠቀምባቸው ስማቸው መነሳት የለበትም? ይህን ለመመለስ የሮኬት ሳይንቲስት ጭንቅላት አይጠይቅም።

በዚህ በእኛው ክፍለ ዘመን የነበሩት አባቶችም ቢሆኑ ፣ ለምሳሌ ከመጀመሪያው ጀምሮ የነበሩት ፓትርያርኮች (ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ) በኦርጋን መጠቀምን ፈቅደው ቤተ ክርስቲያናችን እስከዛሬ ስትገለገልበት ቆይታለች። የሆኖ ሆኖ ይህንን ረብሻ የፈጠሩት የቤተ ክርስቲያኒቷ ተቆርቋሪ ነን ባዮች የቀድሞዎቹም ኾኑ ያሁኑ ቅዱሳን አበው ፈቅደው ሲሠራበት ቆይቶ እስከ እኛ ዘመን የደረሰውን መሣሪያ ለመንቀፍ ፤ በውኑ ከእንዚህ አባቶች በዕውቀታቸውም ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንደርስባቸዋልን ወይም እንበልጣቸዋለን ማለት ትልቅ ድፍረት ፣ ማን አለብኝነት ማለት አይኾንምን? እንዲህ ዐይነቱ ድፍረትና ከእኔ በላይ ዐዋቂ የለም ባይነቱስ ከየት መጣ? እንግዲህ ለዚህ ለተፈጠረው ችግር ዋናው መንስዔ ይህ ድፍረት ነው ቢባል ስሕተት አይሆንም።

_ጸሐፊው በተከታዩ ርዕስ «ምስጢራዊ ትርጉም ስላላቸው» ይልና የጸናጽል ምሳሌን እንዲህ በማለት ያብራራል ፤ «ጸናጽሉን ስናይ የያዕቆብን መሰላል ያስታውሰናል። በጸናጽሉ ላይ የምናያቸው ሁለት ቋሚዎች የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳን ምሳሌዎች ናቸው። ከላይ የምናየው ደጋን መሰል ቅርጽ ሁለቱን ቋሚዎች ያገናኛቸዋል። በመካከሉም መስቀል ቅርጽ ይደረግበታል ደጋኑም የኖኅ ቃል ኪዳን ምሳሌ ነው። እግዚአብሔር በቀስተ ደመና ስሎ የገባለት ቃል ኪዳን ያስታውሰናል። መስቀሉ ደግሞ ተስፋችን በመስቀሉ እንደተፈጸመ ያስረዳናል። ዘመናውያኑ የዘፈን መሣሪያዎች ግን በዚህ መልኩ ከየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ጋር አይዛመዱም ….. » ይላል።_ አሁን እስቲ በማኅሌት ጊዜ መሪጌቶቹ እያዜሙ ጸናጽሉን ሲጸነጽሉ ካህናቱም ይሁኑ ምእምናኑ ይህን ከላይ "<u>በሊቃውንተ ማኅበረ ቅዱሳን</u>" የተዘረዘረውን እያስተዋሉ ነው ብሎ ማሰብ ይቻላል? ለመሆኑ መጀመሪያውኑ ቅዱስ ያሬድ ተጠቅሞበታል ካልንም እርሱ ስለዚህ መሣሪያ እናንተ እንደምትሉት የተናገረበት ቦታ አለ ወይ? ገና ለገና የኦርጋን መሣሪያ ትርጉም የለሽ ነው ለማስባል እንዲህ ዐይነቱን የፈጠራ ገለጻ ማቅረብ አእምሮን ጅምናስቲክ ለማሠራት ካልሆነ በቀር ለመንፈሳዊ ሕይወት የሚፈይደው ምን ነገር አለ?

ስለ መሣሪያ ካነሳን አልቀረ ከዚህ በፊት "ማኅበረ ቅዱሳን" ባዘጋጀው መርሐ ግብር ላይ እንዲሁም በቪዲዮ በተቀናበረ ዝግጅት ላይ ስለ ከበሮ እንዲህ በማለት ሐተታ ሰጥቷል። የከበሮው ቆዳ የተወጠረበት ጠፍር የጌታችንን ግርፋት ያስታውሰናል ፤ እንዲሁም ከበሮው ሲመታ ጌታችን ፊቱን መጸፋቱን ያስታውሰናል ይላል። በመሠረቱ ከበሮም ጸናጽልም ከኦሪቱ ጊዜ ጀምሮ የነበሩ ናቸው ብለናል። ለምሳሌ በመጽሐፈ ሳሙኤል ላይ «ዳዊትና የእስራኤልም ቤት ሁሉ በቅኔና በበገና በመሰንቆም በከበሮም በነጋሪትና በጸናጽል በእግዚአብሔር ፊት በሙሉ ኃይላቸው ይጫወቱ ነበር። (፪ኛ ሳሙ ፮ ፥፭)» ይላል። ታዲህ እኛ ኢትዮጵያውያን ቅድመ

ልደተ ክርስቶስ የኦሪቱን እምነት ተቀብለን ሥርዓቱን ስንፈጽም ከላይ የተገለጹትንም መሣሪያዎች ስንጠቀም ቆይተን ከዚያም ክርስትናን ስንቀበል ብዙውን ሥርዓት ይዘን እስከ አሁን ድረስ አለን። ታዲያ ከበሮ ከኦሪት ጊዜ ጀምሮ የነበረ ሲሆን እንዴት አድርጋችሁ ነው ከክርስቶስ ግርፋትና ጽፋት ጋር ያገናኛችሁት? አባቶቻችን ይህን መሣሪያ ለአገልግሎት እንዲውል ሲያደርጉስ እናንተ የፈጠራችሁትን ገለጻ የት ቦታ ላይ ነው የመዘገቡት? አባቶቻችን ከበሮም ይሁን ጸናጽል በማኅሌቱ ላይ ለመጠቀም የወሰኑት ፤ የዜማ ምትን (Rhythm) ለመጠበቅ ሲባል እንጂ እናንተ ያተታችሁትን ለማሰብ ብለው አይደለም። እንዲያው ይሁን ቢባል እንኳ የሰጣችሁት ሐተታ ሊያስኬድ የሚችለው የሚዜመው ቃለ እግዚአብሔር በሙሉ ስለ ጌታችን መከራ ፤ ሕማም ፣ ስቃይ ብቻ ቢሆን ነበር። ነገር ግን ከበሮው አገልግሎቱ በተለያዩ የጌታ በዓላት ፣ የእመቤታችን እና የሌሎችንም ቅዱሳን ቀን ለማሰብ በሚቆሙ ማኅሌት ላይ ነው። ይህ የሚያሳየው የሰጣችሁት ትርጓሜ አብሮ እንደማይሄድ ነው። ስለዚህ ባጭሩ የቆዳው አገልግሎት የተፈለገውን ድምፅ እንዲያወጣና ካህናቱም ምቱን ተከትለው እንዲያዜሙ ፤ እንዲሁም የግርፋቱ ምሳሌ ነው ያላችሁት ጠፍሩ ደግሞ ዋናው አገልግሎቱ ቆዳውን ለመወጠር ብቻ ነው - በቃ። የእነ መሰንቆ ፣ የእነዋሽንት መሣሪያ ትንታኔስ እንዴት ሆኖ ነው የሚገለጸው? እንዲህ ዐይነቱን ሐተታ ከአባቶች እንደ ተወረሰ አድርጎ በማቅረብ የኦርጋንን መሣሪያነት ለማጣጣል መሞከር ከንቱ ድካም ነው። ዐጉል ተቆርቋሪነት ነው - ወደ ላይ መንጠራራት።

*__በቀጣዩ ርዕስ «አንድ ስለሚያደርገን» በሚለው ስር «በአንድ ወቅት በሐረር አካባቢ የነበሩ ወጣቶች በኦርጋን ይዘምሩ እንደነበረና ይህን ሥርዓታቸውን ወደ ሌላ አካባቢ እንዲዛመት ጥረት አድርገዋል ይላል .......»__*

በመሠረቱ በኦርጋን መዘመር የተጀመረው መንፈሳዊ ኮሌጁን ጨምሮ ፣ ዘመናዊው መንፈሳዊ ትምህርት "ሀ" ብሎ በተጀመረበት በቅ/ሥ/ካቴድራል ፣ በልደታ ፣ በመንበረ ቅዱስ ገብርኤል የዓምደ ሃይማኖት መንፈሳዊ ማኅበር ፣ በምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም ፤ እንዲሁም በሌሎች ቦታዎች የተለመደ እንደነበር አታውቁም ማለት ነው? ይግረማችሁና በምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም ሥር ባለው የተምሮ ማስተማር ማኅበር ኦርጋን እንጂ ከበሮ አይታወቅም ነበር ያን ጊዜ። ታዲያ ያን ጊዜ የተምሮ ማስተማሩ ማኅበር አባላት ታቦት ለማንገስ ወይም ለሌላ መርሐ ግብር ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ሲሄዱ እዚያ በከበሮ ብቻ ለምን ትዘምራላችሁ ፤ ወይም ደግሞ የሌሎች ሰንበት ት/ቤት አባላት ወደ ተምሮ ሲመጡ ለምን በኦርጋን ትዘምራላችሁ የሚል ቅርታ ፣ መከራከር ወይም መነቃቀፍ የሚባል ነገር በዚያን ጊዜ አልነበራቸውም። ለዚህም ቁም ነገር ብሎ ቦታ የሚሰጠው አልነበረም ፤ ሁሉም አገልግሎቱን የሚሰጠው እንደ መሰለው ነበር ፤ መነቃቀፍንና መከፋፈልን ያመጣው ከቀን በኋላ ያለ እኔ ዐዋቂ ፣ ያለ እኔ ተቆርቋሪ ፣ ያለ እኔ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ዐሳቢ ማን አለ ባዩ "ማኅበረ ቅዱሳን" ነው። የዚህ ሁሉ ችግር ጠንሳሹም አራማጁም ይህ

በሰንበት ት/ቤት መምሪያ ሥር የተዋቀረው ድርጅት ነው። "ማኅበረ ቅዱሳን" መስሎና አስመስሎ ወደ ቤተ ክህነቱ ጠጋ እስካለበት ጊዜ ድረስ ፤ በኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲህ ያለ ችግር ፈጽሞ አይታወቅም ነበር።

ጸሐፊው በመቀጠልም *«አንዱ በኦርጋን ሌላው በከበሮ ከሆነ ግን ሰፊ መሠረት ያለው የእምነትና የሥርዓት ልዩነት ይፈጥራል ይላል»።* እንግዲህ ለመንፈሳዊ አገልግሎት የምንጠቀምበትን መሣሪያ እንደ ትልቅ ነገር ቈጥሮ ከሌላ የእምነት ጎራ ውስጥ መጨመር ምን አመጣው? ይህ ደግሞ ጸሐፊው የመሠረታዊ የእምነት ዕውቀት እንደሌለው በግልጽ ያሳየናል ፤ ወይም ደግሞ ሆን ብሎ ምእምናን ለመከፋፈል ያደረገው ተንኰል ነው ከማለት በስተቀር ምን ማለት ይቻላል?!! ጸሐፊው «ቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ስለሰጠባቸው» በሚለው ሥር የተፈቀዱትን መሣሪያዎች ይዘረዝርና *«ከዚህ መመሪያ ወጥቶ በኦርጋን ልዘምር የሚል ካለ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባል አይደለም። የቅዱስ ሲኖዶሱን ውሳኔ በመጣሱም የቅዱሳን ሐዋርያትን ቃል እንዳቃለለ ተቈጥሮ ከምእመናን አንድነት ይለያል» ይላል።* ጸሐፊው እዚህ ላይ ይቅር የማይባል ትልቅ ስሕተት ሲፈጽም ይገኛል። የእምነትና ሥርዓትን ልዩነት እንኳ ለይቶ አለማወቁን ራሱ ይገልጠዋል። የእግዚአብሔር ልጅነት የሚሰጠው ወይም የእሱ ወገን መሆን የሚቻለው እኮ በሰው ሠራሹ መሣሪያ ላይ የሚመሠረት አይደለም ፤ ጸሐፊው ይህ እምነት ካለውማ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣበትን የሰው ልጆችን የማዳን ተልእኮውን ፈጽሞ አያውቀውም ማለት ነው - ትልቅ ጉድለት። በውኑ እግዚአብሔር በኦርጋን ስለተዘመረ ቅር ይለዋል? ወይስ በከበሮና ጽናጽል ስለተዘመረ ከምንም በላይ ይደሰታልን? እናስተውል!!! በጽሑፉ ላይ የተዘረዘው ቀሪ ሐተታ ፍሬ ፈርስኪ በመሆኑ ዝም ብሎ መተው ይመረጣል። መልስ ሊሰጥበት አይገባም - ጊዜ ማጥፋት ይኾናል።

ከዚህ ጽሑፍ በተጨማሪ "የማኅበረ ቅዱሳን" ልሳን የሆነው «ሐመር ልዩ እትሙ ነሐሴ 2001» (11) ላይ መዝሙርና የሙዚቃ መሣሪያዎች በሚል ርእስ የሙዚቃ መሣሪያዎችን አስመልክቶ ሰፊ ሐተታ አቅርቧል። ጽሑፉ ስለ ዜማ ታሪክና ስለ ሌሎችም ነገሮች ያትትና ለምን መሣሪያዎች እንዳልተፈቀዱ ሲያስረዳ «… ሐዲስ ኪዳን የፍጹምነት ዘመን ነው። በመሣሪያ የታጀበ ምስጋና ሳይሆን ነፍስና ሥጋ በአንድነት ተዋሕደው ከልብ የሆነ ምስጋና ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡበት ዘመን ነው። ይህንንም የሚያስረዳን ፥

- በሐዲስ ኪዳንም የዜማ መሣሪያን ስለመጠቀም ምንም ያለመጠቀሱ ፤
- በሐዋርያት ዘመን ምንም ዓይነት የዜማ መሣሪያ ጥቅም ላይ አለመዋሉ



www.ethiopianorthodox.org

- እንደ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅና ቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያ ያሉ ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ፤ እንደ አውሳብዮስ ያሉ የጥንት ቤተ ክርስቲያንን ታሪክ አሳምረው የሚያውቁ የታሪክ አባቶች የዜማ መሣሪያዎች በፍጹም በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ጥቅም ላይ መዋል እንደሌለባቸው ማስተማራቸው።
- በብዙ አብያተ ክርስቲያናት (ግብጽ ፣ ሶርያ ፣ ካቶሊክ ፣ ግሪክ ) የዜማ መሣሪያዎች በቤተ ክርስቲያን የዜማ አገልግሎት ላይ መጠቀም ጥንት የነበረ ሳይሆን በኋላ የተጨመረ ነገር መሆኑን እሱም ጉዳት እያደረሰ መሆኑ ፣
- የመላእክትን ዝማሬ ተምሮ የቤተ ክርስቲያናችንን ዜማ የደረሰው ቅዱስ ያሬድ ምንም ዓይነት የዜማ መሣሪያ አለመጠቀሙ ነው»

***__በሐዲስ ኪዳንም የዜማ መሣሪያን ስለመጠቀም ምንም ያለመጠቀሱ__*** ለሚለው በመሣሪያ አትዘምሩ ተብሏል ለማለት አያስችልም። ምክንያቱም ጌታ ሲመጣ ሊቃነ መላእክቱ የመምጣቱትን ዐዋጅ መለከት እየነፉ መሆኑን ተገልጿል (1ኛ ተሰ 4 ፤16)። ጌታችን በምድር ላይ እያለ ሲያስተምር ሲፈጽም የነበረው ለእኛ አርአያ ለመሆን ከሆነ ፤ እንዲሁም ይህ መሣሪያ ጌታ በዳግም ምጽአቱ ሲመጣ እንደሚጠቀምበት ከተገለጸ እኛ እናንዳንጠቀምበት ጌታ አይፈቅድም ለማለት ያስቸግራል። በተጨማሪም ይህ በአዲስ ኪዳን ያለመጠቀሱ የሚለው አባባል  ጽንሐ ወይም ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውሉ ሌሎችም ዕቃዎች ስላልተገለጹ ልንጠቀምባቸው አይገባም ለማለት መንገድ ይከፍታል።

***__በሐዋርያት ዘመን ምንም ዓይነት የዜማ መሣሪያ ጥቅም ላይ አለመዋሉ__*** - ሐዋርያት በዘመናቸው ወዲህ ከአይሁድ አኩያን ወዲህ ከዓላውያን ነገሥታት ከባድ ተቃውሞ ስለነበረባቸው ቅድሚያ የሰጡት ለስብከተ ወንጌሉ ትምህርት እንጂ ፣ ስለ መዝሙር መሣሪያ አጠቃቀም ለማሰብ ጊዜውም አልፈቀደም ፤ ሁኔታውም አላመቸም። ታዲያ ዛሬ በመዝሙር መሣሪያዎች ላለመጠቀም ይህን ምክንያት አድርጎ ለማቅረብ ማጠፊያው ያጥርባችኋል። ይህ አባባል ደግሞ ኦርጋንን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን ለማንኛውም ዓይነት መሣሪያ የሚመለከት መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። እንደዚህ ከሆነ ደግሞ ከበሮም ጸናጽልም ሌሎችም ተፈቀዱ የምንላቸው ሁሉ መቅረት አለባቸው ማለት ነው። "ማኅበረ ቅዱሳኖች" የሳታችሁት አንድ ዐቢይ ነገር አለ። እዚህ ላይ ሌሎችን ለማስጠላትና ሌላ ስም እየቀጠላችሁ ተቃወምን ስትሉ ፤ በሺህ ከሚቆጠሩ መሪጌቶችና ደብተሮች ጋር ቅራኔ ውስጥ ገብታችሁ ሌላ ጠላት ልታፈሩ ነው-ሳይቸግራችሁ። በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሐዋርያት ታቦት ይዘው እየዞሩ አስተማሩ የሚል አንድም ቦታ አልተጻፈምና ቀስ ብላችሁ ደግሞ  "እኛ



www.ethiopianorthodox.org

ኢትዮጵያውያንም በዚህ መጠቀም የለብንም" ልትሉ እኮ ነው?!! ይህ ደግሞ ወደት ሊያደርሳችሁ እንደሚችል ዐውቃችሁታል?!! የእናንተ ነገር አላርፍ ያለች ጣት .... ሊሆንባችሁ እኮ ነው!!

*<u>እንደ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ፣ እንደ ቀሌሜንጦስ ዘእስክንድርያና አውሳብዮስ</u>* ያሉት አባቶች ከአሕዛብነት ወደ ክርስትና የመጡ ሲሆን ፣ መሣሪያዎች በብሉይ ኪዳን ጊዜ ግልጋሎት ላይ መዋሉንም ቢያውቁ አላበረታቱም። በተጨማሪም የነበሩበት ዘመን ቤተ ክርስቲያን ገና እያደገችና በጣም እየተፈተነች የነበረበት ፤ ብዙ ክርስቲያኖች በእምነታቸው የሚፈተኑበት ነበር ፤ ስለዚህ ዋናው ያተኮሩት መሠረታዊው እምነትን ማስፋፋት እንጂ ስለ ሙዚቃ መሣሪያዎች አጠቃቀም አልነበረም። ይሁን እንጂ በፍትሐ ነገሥቱ (ትእዛዝ ቀኖና 48) ላይ ለተከታይ አባቶች እንደ ኹኔታውና እንደ አስፈላጊነቱ ሥርዓቱን ሊያሻሽሉ እንደሚችሉና ፤ የጎደለም ካለ እንዲያሟሉ ተደንግጓል (12)። ይህም ለቤተ ክርስቲያን ፍጹም ሥልጣን የሚሰጣት መሆኑን አታውቁትም ይሆን?

ቅዱስ ያሬድ ከቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ አንድ ክፍለ ዘመን ቈይቶ የተነሣ ሲሆን ተሰምተው በማይጠገቡት የዜማ ድርሰቶቹ ላይ ስለ አርጋኖንና ስለ ሌሎች የሙዚቃ መሣሪያዎችም እንዲህ በማለት ጽፏል (8) ፥

1ኛ. አስተጋብአተነ ቤት፣ እስመ ለዓለም፥- ሰባኬ ወንጌል ዮሐንስ <u>አርጋኖነ</u> ማኅሌት ዘይደምፅ ለቤተ ክርስቲያን ቀርን ነባቢ ዘይጼውዕ መሐይምናነ ... ትርጓሜው፥- ወንጌልን የሚሰብክ ዮሐንስ ድምጹም በቤተ ክርስቲያን የሚጣፍጥ የማኅሌት አርጋኖን ነው። ዮሐንስ እንደ ቀርነ መለከት ምእመናንን ወደ ቤተ ክርስቲያን ይጋብዛል። (ከዘመነ ልደት ድጓ ጥር 4 ቀን የሚዘመር)

2ኛ. አማኅኩኪ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከብካብ ኮነ በቃና ዘገሊላ <u>ዕንዚራ</u> ደምፀ በዉስተ ጽርሕ... ትርጓሜው፥- ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሆይ እኔ እሰግድልሻለሁ። ክርስቶስ በቃና መንደር ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ በለወጠ ጊዜ ያደረገውን ተአምር እያስታወስሁ በእንዚራ በመቅደሱ እዘምራለሁ። (ከዘመነ ልደት/አስተርእዮ ድጓ፣ በሰንበተ ክርስቲያን ብቻ የሚዘመር፣ ምድቡ ከመወድስ ክፍል)።

3ኛ. ሥረዩ ቤት፣ በሁለት፣ አቡን፣ ስብሕ ወኃይልከ ወኢትምህክ ቃለከ ማዕነቅ ተሰምዐ በምድርነ ዮሐንስኒ ይቤ ከመ ዕንዚራ ዉስተ ጽርሐ ንጉሥ። <u>ትርጓሜ</u>፥- በፍጹም ኃይልህና ድምፅህንም ሳትቆጥብ እግዚአብሔርን አመስግን። መስከረም ስለጠባ ቁራውም በምድራችን እየዘመረ መጣ። ዮሐንስም ይህ መዝሙር በንጉሡ አዳራሽ በእንዚራ እንደሚዘመር ዓይነት ነው ይላል። (ከዘመነ ጽጌ ድጓ፣ ከዘወትሩ አቡን)።

4ኛ. ደብተራ ፍጽምት ዘጸውሊ ለማኅደሩ ዘጽድቅ ዘገብራ ከሃሌ ፈለስት እምዘይበሊ ኀበ ኢይበሊ <u>በመሰንቆሁ</u> እንዘ የሃሊ ዳዊት አቡሃ ዘወልዳ ወዓሊ። <u>ትርጓሜ</u>፥- ቅድስት ማርያም ከሚያልፈው ዓለም ዳዊት በመሰንቆው እየዘመረላት ሳለ ነፍስዋ ከሥጋዋ ተለይታ ወደማያልፈው ዓለም ሄደች። (እግዚሔር ነግሥ፣ ከዘመነ ክረምት ድጓ፣ የእመቤታችን፣ ነሐሴ 16 ቀን)።

5ኛ. ሃሌ ሉያ ለአብ ንሴብሕ ከመ ቀስተ ደመና ዘአሜ ክረምት አክሊል ንጹሕ ዲበ ርዕሶሙ ሃሌ ሉያ ለወልድ ንዜምር ሃሌ ሉያ ወለመንፈስ ቅዱስ ንሴብሕ ወንዜምር ኪያሁ መድኅነ ከመ ዝበጠተ <u>መሰንቆ አርጋኖን</u> ስብሐቶሙ ለእሙንቱ ካህናት። <u>ትርጉም</u>፡- እንደ ክረምት ቀስተ ደመና ንጽሕ አክሊልን ለካህናት ያዘጋጀ እግዚአብሔር አብን፣ እግዚአብሔር ወልድንና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን እናመሰግናለን። ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡበት የካህናት ምሥጋናም በመሰንቆና በአርጋኖን እንደሚዘመር መዝሙር ጣዕመ ዜማው ማራኪ ነው። (ከጾም ምዕራፍ የማክሰኞ አርያም)። (8) እንግዲህ ያሬድ ወደ ሰማይ ተነጥቆ በተወሰደ ጊዜ ውብ የሆነውን የመላእክት ምስጋና በአርጋኖን ታጅበው ሲዘምሩ መስማቱን ገልጾ ምስጋናውንም በሰማቸው መሣሪያዎች መስሎ የዜማ ድርሰቱን ትቶልን አልፏል። ታዲያ በሰማይ መላእክት እንደዚያ በመሣሪያ ያመሰግናሉ ከተባለ በውኑ እግዚአብሔር አምላክ ሰዎች በምድር ላይ በተመሳሳይ መሣሪያ አያመስግኑ ይላልን?

ስለዚህ ሐዋርያት በዘመናቸው ቀጥሎም ከእነርሱ በኋላ የተነሱት አባቶች ለረጅም ዘመናት መሣሪያ ያልተጠቀሙ ቢሆኑም ፤ ቆይተው የተነሡ አባቶች ግን ወቅቱ በፈቀደ ጊዜ መሣሪያዎቹ ግልጋሎት ላይ እንዲውሉ አድርገዋል ምክንያቱም እነርሱም እንደቀደሙት አባቶች በአንብሮተ እድ ተሹመዋልና።

***<u>በብዙ አብያተ ክርስቲያናት (ግብጽ ፣ ሶርያ ፣ ካቶሊክ ፣ ግሪክ ) የዜማ መሣሪያዎች በቤተ ክርስቲያን የዜማ አገልግሎት ላይ መጠቀም ጥንት የነበረ ሳይሆን በኋላ የተጨመረ ነገር መሆኑን እሱም ጉዳት እያደረሰ መሆኑ ፣</u>*** ምን ዐይነት ጉዳት? ልትገልጹት ትችላላችሁ? በመሠረቱ ይህ አባባል የፈጠራ እንጂ ትክክለኛ አይደለም። እንዲያውም የግብጽም (13) ሆነ የራሽያ አብያተ ክርስቲያናት (14) ፣ እዚህ ዌብ ሳይት ላይ እንዳደረግነው ፣ በዌብ ሳይታቸው ላይ መዝሙራቸውን በመሣሪያ የታጀበና ያለመሣሪያም በድምፅ ብቻ አድርገው አስቀምጠውታል። ይኸ የሚያሳየው ደግሞ እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት በመሣሪያ የታጀቡ መዝሙራት የበለጠ እንዲስፋፉ ያላቸውን ፍላጎት እንጂ ጉዳት ማድረሳቸውን አይደለም።

በዚሁ ጽሑፍ ላይ የሙዚቃ መሣሪያ መጠቀም የለብንም ተብሎ የተሰጠው ሌላው ምክንያት «የቅዱስ ያሬድ ድርሰቶች በርካታ ድምፆች ስላሉት በመሣሪያዎቹ ሙሉ በሙሉ መጫወት አይቻልም ነው።» በመሠረቱ ይህን የቅዱስ ያሬድን ዜማ ለመጫወት የሚሞክሩት ብዙዎቹ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ዜማ ጋር ትውውቅ ስለሌላቸው ነው እንጂ ዜማውን ለመጫወት አስቸጋሪ ሆኖ አይደለም። በ2002 በመዝሙረ ተዋሕዶ ቁጥር

4 ላይ የወጣውን «አማን በአማን» የሚለውን ዜማ እንድትሰሙት እጋብዛለሁ (15)። እንዲያውም የሚያስደንቀው በ6ኛው ክፍለ ዘመን ቅዱስ ያሬድ የደረሰው ዜማ ስታይል ከእርሱ በኋላ በአውሮጳ ከተነሱት የክላሲካል ሙዚቃ ደራሲዎች ጋር ተመሳሳይነት አለው (16)። ስለሆነም ዜማውን የበለጠ ልናስተዋውቀው ይገባል እንጂ የተለያዩ ሰበብ እየሰጠን በሀገራችን ብቻ ተወስኖ እንዲቀር ማድረግ የለብንም።

ቅዳሴን በተመለከተ የተዘረዘረው ሐተታ <u>«ኦርጋኑ በምስባክ ጊዜ ጥቅም ላይ በዋለበት ጊዜ ምስባኩ ምልክቱን ጠብቆ በትክክል ሲዜም ፒያኖው ማጀብ ስለማይችል ዜማው ያለምልክቱ ይለጠጥ ነበር .....»</u> ይኼ አባባል እንኳ አያስኬድም ምክንያቱም የቅዳሴ ዜማ በግእዝና በዕዝል ስለሆነ አለምንም ችግር ሙሉ በሙሉ ለመጫወት አያስቸግርም። መሣሪያውን በትክክል ከዜማው ጋር አመሳስሎ ለመጫወት የሚያስፈልገው ፤ መሣሪያውን የሚጫወተው ሰው ዜማውን በደንብ ማወቅ ብቻ ነው። ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ የመጀመሪያው ካሴቱ ላይ «እስመ መምህረ ሕግ» (17) ብሎ ያዜመውን መስማት በቂ ነው። በተጨማሪም ከላይ የተሰጠው አስተያየት ውድቅ እንደሆነ እንድታውቁት እናንተው ሰምታችሁ እንድትፈርዱ ሌላ ምስባክና (18) ሙሉ ቅዳሴውን በኦርጋን የታጀበ እዚህ ላይ አውጥተናል (19)። ይህ እንድታደምጡት እንጂ ቅዳሴው በኦርጋን ይቀደስ ለማለት አይደለም። እንዲሁም የሰዓታት ዜማ ቢሆን በመሣሪያ አጅቦ ለመጫወት ምንም አስቸጋሪ እንዳልሆነ ታዳምጡት ዘንድ ይኸው ቀርቧል።(20)

በአጠቃላይ ለዚህ ሁሉ ለተፈጠረው ትልቅ ጥፋት ወይም ስሕተት ዋናው ተጠያቂ ከበላይ ያሉት አባቶች ወይም ደግሞ በወቅቱ የነበረው የሰንበት ት/ቤት መመሪያ ኃላፊ ነው። እንዲህ ዓይነት ጽሑፍ ሲጻፍ በወቅቱ ተው እንደሱ አይደለም ቢሏቸው ኖሮ አሁን አለንበት ሁኔታ ላይ ባልተደረሰ ነበር። ቤተ ክህነቱ ቀደም ሲል ተገቢውን ቁጥጥር ቢያደርግ ኖሮ ፤ በአለፈው ዓመት መንግሥት በቤተ ክህነትና በማኅበረ ቅዱሳን መካካል በተፈጠረው ግጭት ጣልቃ ገብቶ «ማኅበረ ቅዱሳንን» እስከ ማስጠንቀቅ ባልደረሰም ነበር። ከተዘረዘሩት ዐበይት ችግሮች አንዱ «ማኅበረ ቅዱሳን በማናለብኝነት እያሳተመ በሚያሰራጫቸው ጽሑፎቹ በማያገባው እየገባ መንግሥትን ፣ ሕዝብን እንዲሁም ቤተ ክርስቲያንን የሚያጋጭና የሚያለያይ ተገቢ ያልሆኑ ድርጊቶች ስለፈጸመ እንደነበር ሰነዶች ያስረዳሉ (21)። እነዚህ ድርጊቶች አሁንም መቀጠል የለባቸውም። ይህ እኩይ ድርጊት ከሰው ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔርም የሚያጣላችሁ ነው።

ከላይ እንዳየነው አርጋኖን ከ1940ዎቹ ጀምሮ የቤተ ክርስቲያኒቱ የበላይ የሆኑትን የብፁዓን ቅዱሳን አባቶቻችንን ይሁኝታ አግኝቶ አገልግሎት ሲሰጥ መኖሩ ግልጽ ነው። ከ1986 በኋላ ግን ያልሆነውን

እንደሆነ ፤ ያልተባለውን እንደተባለ አስመስሎ በመናገር በሀገር ቤት የሀገር ባሕል መሣሪያ ከበሮና ሌሎች መሣሪያዎች ብቻ ናቸው ማለቱ ፤ ኦርጋን በፍጹም በቤተ ክርስቲያናችን አገልግሎት ውሎ እንደማያውቅ አድርጎ በሐሰት መጻፍ- መናገሩ አሳፋሪ ድርጊት ነው። የሲኖዶሱንም ውሳኔ አጣሞ እንደማስረጃ አድርጎ ማቅረቡ ትልቅ ድፍረት ነው ፤ ሕሊና ላለውም አሳፋሪ ነው። እዚህ ላይ ማብቃት አለበት።

በመሠረቱ ክራር ከዜማ አጃቢ መሣሪያዎች እንደ አንዱ ኾኖ ያገለግል ዘንድ በቅዱስ ሲኖዶስ አልተፈቀደም ፤ ወይም አልተወሰነም ፤ በእናንተ በኩል ተዘጋጅተው የሚቀርቡት አብዛኛዎቹ ካሴቶችና ቪዲዩዎች ግን እየተጠቀማችሁበት ነው። እዚህ ላይ ሳይጠቀስ የማይታለፍ አንድ ቁም ነገር አለ ፤ ክራር በቀድሞ ጊዜ በሀገራችን ፋኖዎች ለዐደን በረሃ ወርደው የሚያንጎራጉሩበት ፣ ወኔያቸውን የሚያነሱበት ፣ የከተማ አውደልዳዮች ቅሬዎች የሚሞካሸሹበት የዓለማዊ መሣሪያ ነው። ዋሽንት ደግሞ የሚታወቀው በእረኞች መሣሪያነቱ ነው። እዚህ ላይ ማኅበረ ቅዱሳን ሲፈልገው ሲኖዶስ እንዲህ ብሎ ወስኗል በማለት ሌሎችን ለማሳደድ ይጠቀምበታል ፤ ሳይፈልግ ደግሞ በራሱ ፈቃድ ልክ እንደ ክራሩ እኛ ካልን ሲኖዶስም አያገባውም በሚል በራሱ አስተሳሰብ የሚራመድ ድርጅት ነው።

<u>ኦርጋንን ብቻ ዓለማዊ መሣሪያ አድርጎ ነቅፎ ክራርን ፣ መሰንቆን ፣ ዋሽንትን የመሳሰሉትን ደግሞ የመንፈሣዊ መዝሙር አጃቢ መሣሪያዎች አድርጎ ማቅረብ ያሳፍራል ፤ ምክንያቱም እነዚህ የሀገር ባህል መሣሪያዎች በብዛት ከጠጅ ቤት አንስቶ እስከ ትልቁ የሙዚቃ ዝግጅቶች ላይ ዓለማዊ ዘፈኖች የሚቀነባበሩባቸው መሣሪያዎች ናቸውና። ዋናው ቁም ነገሩ ግን እንደ አጠቃቀማችን ነው።</u> አንዳንዶች በአሁን ዘመን ኦርጋን መጠቀም እየቀረ ስለመጣ በቃ አያስፈልግም በማለት ግትር የሆነ አስተያየት ይሰጣሉ ፤ ከዚያም አልፎ የሚያዳምጡትን ሁሉ እስከመኮነን ይደርሳሉ። እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ለዚህ ሁሉ መከፋፈል ምክንያት የሆነው ማኅበረ ቅዱሳን ዝም በመባሉ ፣ ምእመናንን ሊከፋፍላቸው ችሏል። አሁንም ይህ ማኅበር ያደረሰው ችግር ዝም ብሎ ከታለፈ ወደፊት የበለጠ ችግር ሊያመጣ እንደሚችል በማመን ለማሳሰብ ነው።

በመዝሙረ ዳዊት 148 ላይ ሥነ ፍጥረት በሙሉ ልዑል እግዚአብሔርን እንደሚያመሰግን ተጽፏል። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ከበሮም ሆነ ጸናጽል ፣ መሰንቆም ሆነ ዋሽንት ክራርም ሆነ ሌላ ማናቸውም የሙዚቃ መሣሪያ እንደአስፈላጊነታቸው ለመንፈሳዊ አገልግሎት ብንጠቀምባቸው እኛን ደስ ካሰኙን ዋናው ቁም ነገሩ እዚያ ላይ ነው። እዚህ ላይ አንድ ነገር ልበል!! ሰው ሠራሽ የኾኑት እነዚህ መሣሪያዎችና የመሳሰሉት ብቻ ሳይሆኑ ፍጥረተ ዓለም (Universe) ራሱ በውስጥም ፣ በአፍአም ዕጹብ ድንቅ በሆነ ጣዕመ ዝማሬ ተቃኝቶ

ያለ ዕረፍት በመንቀሳቀስ የልዑል እግዚአብሔርን ክብርና ታላቅነት በውዳሴ ፣ በቅዳሴ ፣ በስባሔ አዎን ያለ ዕረፍት ሲያመሰግን እንደሚኖር የምናውቅ ስንቶቻችን ነን?! ታዲያ ስለ አምላካችን ክብር ለምናቀርበው ምስጋና በዚህ ወይም በእዚያ መሣሪያ መሆን አለበት እንል ዘንድ እኛ ማን ነን?!!!

www.ethiopianorthodox.org team!

**ኅዳር 2003**

## ዋቢ መጻሕፍት

1 መዝሙረ ጸሎት -የመጀመሪያው የመዝሙር መጽሐፍ በኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን (1940)

1A እንደ ቸርነትህ

2 የአንደኛ ክፍለ ጦር የዘመሩት መዝሙራት

3 በቀድሞ ጊዜ በዘመናዊ መሣሪያ ለዘመሩ ከቤተ ክርስቲያን ይሰጥ የነበረ የምስክር ወረቀት

4 የዘወትርና የበዓላት መዝሙራት

5 ሐመር መጽሔት 1995

6 የኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን ድኅረ ገጽ

7 የአርጋኖን መሣሪያ ትርጓሜ - መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ

8 የመዝሙር መሣሪያ ታሪካዊ አመጣጥ

9 መዝሙር እና የመዝሙር መሣሪያዎች

10 መጽሐፈ አርጋኖን

11 መዝሙርና የሙዚቃ መሣሪያዎች (ልዩ እትም ነሐሴ 2001)

12 ፍትሐ ነገሥት

13 የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ድኅረ ገጽ

14 የራሺያ ቤተ ክርስቲያን ድኅረ ገጽ - http://www.myocn.com/ark/

15 ከቅዱስ ያሬድ ዜማ "እማን በአማን" ያዳምጡ

16 የቅዱስ ያሬድ ታሪክ

17 እስመ መምህረ ሕግ ያዳምጡ

18 ምስባክ በአርጋኖን ያዳምጡ - የገና

18a ምስባክ በአርጋኖን ያዳምጡ - የጥምቀት

19 ቅዳሴ ዜማ በአርጋኖን የታጀበ ያዳምጡ

20 ሰዓታት ዜማ በአርጋኖን የታጀበ ያዳምጡ

21 የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ በማኅበረ ቅዱሳን ላይ ያስተላለፈው ውሳኔ